የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

## የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ( ወክንድ )

## ለአዛውንት ጀግኖችና አርበኞች የአክብሮት ዕውቅና ይሰጣል

ወክንድ ከተመሠረተባቸው ዋናዋና ዓላማዎቹ መካከል÷ ለአዛውንት ጀግኖችና አርበኞች ምስጋና÷ አክብሮ
ትና ዕውቅና መስጠት ከፍተኛውን ቦታ ይዟል ። ይህችን ታሪካዊ ሀገር በነፃነቷ ታፍራና ተከብራ እንድትቆ
ይ አድርገው ለዚህ ለኛው ትውልድ አስረክበው ያለፉትንም ሆኑ አሁንም በሕይወት ያሉትን አርበኞች እያከ
በሩ ዕውቅና መስጠትና የሚገባቸውን ምስጋና ማቅረብ የወክንድ ቋሚና ዓይነተኛ ተግባሩ እንደሆነ እናም
ናለን ። በመሆኑም በዘንድሮው 2002 ዓም በዓላችን ሁለት ታላላቅ ጀግኖች አዛውንትን በማክብር ÷ አመስግ
ነን ዕውቅና ለምስጠት ወስነናል።እኚህ ጀግኖቻችን ኮሎኔል አስናቀ እንግዳና ኮሎኔል ዕምሩ ወንዴ ናቸው ።

### አንደኛ ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ፡-

በአስራ ዘጠኝ መቶ 28 ዓም ፋሽስት ኢጣሊያ ሀገራችንን በወረረበት ወቅት ወራሪውን ጦር ከሀገር ለማ
ስወጣት በተደረገው የአምስት ዓመት የአርበኝነት ተጋድሎ በግንባር ቀደም

ተዋግተው ኢትዮጵያ ሀገራችንን ነፃ ከወጧት አርበኞች አንዱ ናቸው።

ጠላት ከሀገራችን ከተባረረ በኋላም÷ለሕዝብ ነፃነት÷ለዴሞክራሲ ሥርዓትና ለዕድግት ሲባል

ከለወጥ ፈለጊው ክፍል ጋር በመሆን የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት በመቃዎማቸው ለአምስት ዓመ
ታት ያህል ዓለም በቀኝ ወኅኒ ቤት ታስረው ተሰቃይተዋል። ቤተሰባቸውም ብዙ ፍዳን ተቀብሏል።

በአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድስት ዓም ሕዝባዊ አመፅ ወቅት የደርግን ፋሽስታዊ አገዛዝ በመቃወም ወደ
ትግሉ ሜዳ በመግባት ከኢሕአፓ ጋርና በሀገርወዳድ ድርጅት መሰራችነት ደረጃም ለአስራ ሰባት ዓመታት የ
ሕዝብ ወገን መሆናቸውን በተግባር ገልጸዋል። ለዴሞክራሲ ሥርዓት ያላቸውን ጽኑ ዕምነት እስርና
እንግልት የማይበግረው መሆኑን በትግል አስመስክረዋል ።

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

የወያኔን ማንነተና ምንነት አስቀድመው ያውቁ ስለነበር፣ የዚህ ዘረኛ ሥርዓት አራማጆች በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትሉትን ጥፋት ከተረዱት ጥቂት አስተዋዮች መካከል አንዱ

ኮሎኔል አስናቀ ናቸው:: በመሆኑም ወያኔን በመቃወም ለመሰደድ በቅተዋል:: በስደትም ሆነው ተቀዋሚ ድርጅቶችን ለማስማማት ሲል ጉባዔ አበው የሚባል ተቋም በመመስረት የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል:: የወያኔን ሥርዓት በመቃወምም በርካታ ታሪካዊ ሰነዶችን ፥መግለጫዎችንና ጽሁፎችን አውጥተዋል::

ዓላማቸውንና ዕምነታቸውን የሚገልጹ በርካታ መጻሕፍትን ደርሰዋል :: በሴቶች ላይ የሚደርሰውንም በደል በሚገባ በመፅሐፍ አጋልጠዋል:: ሕይወታቸውን በሙሉ በታገሉላትና በተሰውላት ሀገራቸው መኖር ሲገባቸው በዚህ አዛውንት ዕድሜያቸው በስደት የሚንገላቱ መሆናቸው ቢያሳዝነንም፥ ለወጣቱ ትውልድ ባሳዩት የአርበኝነትና ቆራጥና ፅኑ የትግል አርዓያነታቸው እናከብራቸዋልን::በመሆኑም ዕውቅና ስንሰጣቸው ከታላቅ አክብሮትጋር ብቻ ሳይሆን፥ ዓርአያነታቸውንም ለመከተል ቃል እየገባን ነው ::

<u>ለሁለተኛ ኮሎኔል ዕምሩ ወንዴ</u> :-

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለውጥ ያስፈልጋታል ብለው ከተነሱት ተራማጅና ዴሞክራሲያውያን መኮንኖች መካከል የመጀመሪያውን ረድፍ ያየዙት ኮሎኔል ዕምሩ ወንዴ፥ከአምሳ ዓመታትባላነሰ ዘመን ሀገራችውን በሀገር መከላካያ ረድፍ በሚያኮራ ሁኔታ አገልግለዋል :: የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት በመቃወም የኢትዮጵያ አስተዳደር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል ብለው በመነሳታቸው ፥ ለአምስት ዓመታት ያህል በዓለም በቃኝ ወኅኒ ቤት ታስረው ተሰቃይተዋል:: ቤተሰባቸውም አብሮ ተሰቃይቷል:: ታስረው ከተፈቱም በኋላበሀገሪቱ ውስጥ ሥራ እንዳያገኙ ተከልክለዋል:: ኮለኔል ዕምሩ ግዳጅ ተቀብለው ወደ ኮሪያም ወደ ኮንጎም የዘመቱ መኮንን ናቸው::

በአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድስት ዓም የሀገራችን ዐብዮት ወቅት የደርግን ፋሽስታዊ አገዛዝበፅኑ በመቃወማቸው ወደ ወኅኔ ተወርውረው ተሰቃይተዋል :: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸው ወገንተኝነት የማይገበገር በመሆኑ ፥ደርግ በሹመት ሊደልላቸው ቢሞክርም ፅኑ ዓላማቸውንና ሕዝባዊነታቸውን በጭብጥ ምስር ሊለውጡ አልፈለጉም :: ይልቁንም፥ ወደ ኢሕአፓ ትግል ሜዳ ገብተውና በሀገር ወዳድ ድርጅት መስራችነት ደርግን ለአስራ ሰባት ዓመታት ሲፋለሙት ቆይተዋል:: የዓላማ ጽናት ምን እንደሆነም በተግባር አስመስክረዋል :: ብዙ መሥዋዕትም ከፍለውበታል::

ወያኔ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በሽግግሩ ወቅት እንዲተባበሩት አማላጅ ቢልክባቸውም ኢትዮጵያን በዕቅ
ድ ከሚያጠፉ ቡድን ጋር እንደማይተባበሩ ተናግረው ኢትዮጵያን ለማዳን ከሚታገለው ኃይል ጋር ተባብረው
በመቆም ዘመን የማይሽረውን ሀገር ወዳድነታቸውንና አርበኝነታቸውን በድጋሜ አስመስክረዋል ። ለዚህ
ም ዓላማ በኢትዮጵያ ጠረፎችና በሱዳን ውስጥም በስደት ተሰቃይተዋል። ፅኑ ፍዳም ተቀብለዋል።

ኮሎኔል ዕምሩ ወንዴ ለአለፉት አርባ ዓመታት በሀገራችን የተፈራረቁትን ሦስት አምባገነንሥርዓቶች በፅኑ
የተቀወሙ ፥ የታገሉና አይከፍሉ መሥዋዕት የከፈሉ በመሆናቸው ለዓርዓያነታቸው ወክንድ ዕውቅና
ውን ከከፍተኛ አክብሮትና ምስጋና ሰጥቷቸዋል።

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com